# የዜጎች መድረክ

ኢዜማ

ቅፅ 2 ቁጥር 72 ጥር 12 ቀን 2013ዓ.ም

በኢዜማ ህዝብ ግንኙነት የሚዘጋጅ

# ትኩረት የተነፈጋቸው የሡነ - ሕዝብ ጉዳዮች

መሳይ ግርማ



# ቆይታ

## ‹‹ብዙዎቹ ፖለቲከኞች፣ ወይም የፖለቲካ ፓርቲዎች ቀና ማለት፣ ቀጥ ማለት አይሞክሩም፡፡››

### ወሰንሰገድ ገብረ ኪዳን (ጋዜጠኛ)

ጋዜጠኛ ወሰንሰገድ ገ/ኪዳን ከ1989 ዓ.ም ጀምሮ በጋዜጠኝነት ሙያ ላይ ተሰማርቶ ይገኛል። ከ1989 መጨረሻ እስከ 1997 አጋማሽ በ "ኢትኦጵ" ጋዜጣ እና መፅሔት በምክትል እና በዋና አዘጋጅነት፣ ከ1997 አጋማሽ እስከ ጥቅምት 1998 በ ‹‹አዲስ ዜና›› ጋዜጣ ዋና አዘጋጅነት ሰርቷል። ወሰንሰገድ በ1997 ዓ.ም ምርጫ ከቅንጅት መሪዎች ጋር ከተከሰሱ እና ከታሰሩ ጋዜጠኞች አንዱ ነው። ከሁለት ዓመት እስር በኋላ ከቃሊቲ ሲወጣ ‹‹ሐራምቤ›› የተሰኘ ጋዜጣ ማሳተም ጀምሮ በተለያየ ተግዳሮቶች ምክንያት ከተዘጋ በኋላ በ ‹‹አውራምባ›› ጋዜጣ ላይ ሰርቷል። አሁንም ለተለያዩ የሕትመት ውጤቶች፤ መጣጥፎችን በመፃፍ ላይ ይገኛል። ወሰንሰገድ ገ/ኪዳን ሶስት መፅሐፎችን ለሕትመት አብቅቷል። በ2004 ዓም፤ የእስር ቤት ሕይወትን የሚተርከው ‹‹የቃሊቲ ምስጢሮች›› በ2006 ዓ.ም ‹‹ሕዝብ ማለት›› የምትል የግጥም መድበል፣ በያዝነው የ2013 ዓመት ደግሞ ‹‹ነፃነት›› የተሰኘ የግጥም እና የወግ ስብስብ መፅሐፍ ለንባብ አብቅቷል። ወሰንሰገድ የዚህ ሳምንት የዜጎች መድረክ የ ‹‹ቆይታ›› አምድ እንግዳ ነው፡፡ ቆይታችንን አብራችሁ ትካፈሉ ዘንድ እንጋብዛለን፡፡



*ጨዋታችንን ለመጀመር በመሠረቱ ጋዜጠኛ አንቱ አይባልም በየትኛው እንቀጥል?*

ለውይይታችን ቅለት ሲባል አንተ ብትለኝ ይሻላል፡፡

*ኢዜማ ከተመሠረተበት ጊዜ ጀምሮ በተለያዩ ወገኖች ከፍተኛ ትችት ይቀርብበታል፡፡ ይኼን ያህል ወቀሳ የሚደርስበት ለምን ይመስልሃል?*

ለምን ይመስለኛል መሰለህ? ከግማሽ ምዕተ ዓመት በላይ የዘለቀው የኢትዮጵያ የፖለቲካ ባህል ጠማማ ሆኖ የበቀለ በመሆኑ ነው፡፡ የፖለቲከኞቻችን ዕይታ አጭር በመሆኑ ነው፡፡ አጭር ስልህ፤ ከዘላቂ የሀገር ጥቅም ይልቅ የራስን ጥቅም ያስቀደመ በመሆኑ ነው፡፡ በዚህም የተነሳ ፖለቲካችን መጠላለፍ፣ መጣጣል፣ መካሰስ፣ መገዳደል ሆኖ ነው ከግማሽ ምዕተ ዓመት በላይ የዘለቀው፡፡

እንደውም እዚህ ላይ የአጫጭሮቹ እና ጎባጦቹን ዛፎች ታሪክ ብነግርህ ይሻላል፡፡ ነገርዬው የአንድ ጥንታዊ ፈላስፋ አስተምህሮ ነው፡፡ አስተምሮቱ በዴሞክራሲ ዙሪያ ያጠነጠነ ነበር፡፡ በደን ጥቅጥቅ ያለን አንድ ተራራ እያመለከተ "ይታያችኋል ያ በደን ጥቅጥቅ ያለ ተራራ!... እዚያ ተራራ ውስጥ የበቀሉት ሁለት ዓይነት ዛፎች ናቸው፡፡ እጅግ ረዣዥም እና ቀጥ ቀጥ ያሉ፤ እንዲሁም እጅግ አጫጭር እና ጎባጣ ዛፎች ናቸው ተራራውን የሸፈኑት፡፡ ..." አለ፡፡

አጫጭሮቹና ጎባጦቹ መብታችን ተነፈግን ባዮች ናቸው፡፡ ማነው መብታችሁን የነፈገው? ሲባሉ ረዣዥሞቹና ቀጥ ቀጥ ያሉ ዛፎች ናቸው ይላሉ፡፡ ምክንያቱም እጅግ ቀጥ ቀጥ ያሉ የረዘሙ በመሆናቸው፣ ከእኛ ቀድመው ንፋስ፣ ዝናብና ፀሐይ ያገኛሉ፡፡ ስራቸውም እጅግ ረዣዥም በመሆኑ ከእኛ ቀድመው ለዛፎች ዕድገት የሚያስፈልገንን የምድርን ማዕድን ይሰበስባሉ፡፡ በዚህ የተነሳ ነው እኛ አጭርና ጎባጣ ለመሆነው የበቃነው ይላሉ፡፡

እዚያ ጥቅጥቅ ያለ ደን ውስጥ የሚመላለስ አንድ ገበሬ አለ፡፡ እሱ ብቻ ወደዚያ ደን ለምን እንደሚመላለስ ዛፎቹ ሁሉ ያውቃሉ፡፡ በገበሬው ወደዚያ ተራራ ጎራ ማለት ይበልጥ የሚደሰቱት ግን አጫጭሮቹና ጎባጦቹ ዛፎች ናቸው ፡፡ ምክንያቱም ያ ገበሬ ወደዚያ ተራራ የሚዘልቀው የመጥረቢያ ዛቢያ ለመቁረጥ ነው፡፡ ለመጥረቢያ ዛቢያነት የሚሆኑት ደግሞ እነሱዉ ናቸው ፡- አጠርና ጎበጥ ያሉ በመሆናቸው፡፡ ቀድሞ የሚቆርጣቸውም እነሱኑ ነው፡፡ ቢሆንም በገበሬው መምጣት እጅጉን ይደሰታሉ፡፡

አጫጭሮቹ ዛፎች፣ ገበሬው አስቀድሞ እነሱን እንደሚቆርጥ እያወቁ በደስታ የሚፍነከነኩት ለምን መሰለህ?፤.... ገና ለገና ተቆርጠው፤ ገና ለገና የመጥረቢያ ዛቢያ ሆነው፤ ገና ለገና ገበሬው እጅ ላይ ውለው፤ ገና ለገና ረዣዥምና ቀጥ ቀጥ ያሉትን ዛፎች ገንድሰው መጣልን ስለሚያልሙ ነው ይላል ፈላስፋው በአስተምህሮቱ፡፡

ልክ እንደዚህ ነው የኛ ሀገር ፖለቲካ ፡፡ ጎባጣ ነው፡፡ ብዙዎቹ ፖለቲከኞች፣ ወይም የፖለቲካ ፓርቲዎች ቀና ማለት፣ ቀጥ ማለት አይሞክሩም፡፡ ከዚያ ይልቅ ቀጥ ያለ ካለ፣ የተቃና ካለ ስሙን ማጠልሸት፣ መክሰስ፣ መፈረጅ፣ እሱን መገዝገዝና መጣል ነው የሚቀናቸው፤ ያለፍንበት የፖለቲካ ባህል ይህንን ዓይነት ነው፡፡ ኢዜማም የገጠመው ተግዳሮት ከዚህ የተለየ አይደለም ፡፡ የሚወቀሰውም፣ የሚከሰሰውም ከዚያ የጎበጠና የተጣመመ የፖለቲካ ባህላችን የተላቀቅን ባለመሆኑ ነው፡፡

> ‹‹ብዙዎቹ ፖለቲከኞች፣ ወይም የፖለቲካ ፓርቲዎች ቀና ማለት፣ ቀጥ ማለት አይሞክሩም፡፡ ከዚያ ይልቅ ቀጥ ያለ ካለ፣ የተቃና ካለ ስሙን ማጠልሸት፣ መክሰስ፣ መፈረጅ፣ እሱን መገዝገዝና መጣል ነው የሚቀናቸው፤ ያለፍንበት የፖለቲካ ባህል ይህንን ዓይነት ነው፡፡››

*ኢዜማ ከፍተኛው የመንግሥት ኃላፊነት በሕዝብ በቀጥታ ምርጫ ፕሬዝዳንታዊ ሥርዓት እንዲሆን አበክሬ እሰራለሁ ይላል ፡፡ ይህንን እንዴት ትመለከተዋለህ?*

ጥሩ ነው፡፡ እሱ ግን ዘንቦ ተባርቆ የሚመጣ ነው፡፡ ከጠንካራ ትግል በኋላ ሊሆን የሚችል ነው፡፡ በቅድሚያ ኢዜማ ሊሰራቸው የሚገባቸው ጉዳዮች አሉ፡፡ እጅግ በጣም ፈታኝ ሥራዎች፡፡ በቅድሚያ እነዚያን ፈታኝ ሥራዎች ሰርቶ በምርጫ ማሸነፍ አለበት ፡፡ አብላጫውን የምክር ቤት ወንበር መያዝ አለበት፡፡ ከዚያም ሕገ መንግሥቱን ማሻሻል ወይም መቀየር አለበት ፡፡ ሕገ መንግሥቱን የመቀየር አቅም ሳይኖረው ፕሬዝዳንታዊ ሥርዓት ሊያመጣ አይችልም፡፡ እዚህ ላይ ፕሬዝዳንታዊ ሥርዓት አይበጅም እያልኩህ አይደለም፡፡ ይጠቅማል፡፡ በሕግ አውጪ፣ በሕግ


## አድራሻ

ስልክ
+251118592950

ኢሜይል
ethzema@gmail.com

ትዊተር
www.twitter.com/ethzema

ፌስቡክ
www.facebook.com/ethzema

የኢትዮጵያ ዜጎች
ለማኅበራዊ ፍትህ
(ኢዜማ)

ጥር 12 ቀን 20113 ዓ.ም
አዲስ አበባ

አስፈፃሚ፣ በሕግ ተርጓሚ እውነተኛ የሆነ ነፃነት ያስገኛል፡፡ ነፃነታቸው እንደ ኢህአዴግ ዘመን የይስሙላ አይሆንም ማለት ነው፡፡ ብሔርተኝነትን እያከሰመ ሀገራዊ አንድነትን ሊያጠናክር ይችላል፡፡ ነገር ግን አሁን ካለንበት ወቅት አንፃር ነገርየው ብዙም አንገብጋቢ አይመስለኝም፡፡ አሁን ለኢዜማ አንገብጋቢ መሆን ያለበት ከፊቱ ያለው ምርጫ ይመስለኛል፡፡

*ሰንደቅ ዓላማን በተመለከተ ሶስቱን ቀለማት መርጦ አርማ የሚያስፈልገው ከሆነ በሕዝብ ይሁንታ የሚወሰን ይሆናል ይላል፡፡ እዚህስ ላይ ምን ትላለህ?*

እ ....... ይኼ አንቀፅ እንኳን ብዙም አልጣመኝም፡፡ ማለቴ ግልፅ አይደለም ፡፡ ኢዜማ በሕዝብ ይሁንታ ሲል ምን ማለቱ ነው? ይሁንታን በምን መልኩ ነው የሚበይነው፡፡ ሕዝብ ይሁንታ የሚሰጠው ተሰብስቦ ነው ወይስ በምርጫ ዓይነት ሲስተም? ግልፅ አይደለም፡፡

እንደኔ እንደኔ ፓርቲዎች አንዳንድ ጉዳዮችን ወደ ሕዝብ መግፋት ያለባቸው አይመስለኝም፡፡ ሕዝብን የጉዳዮ መሸሸጊያ ማድረግ ያለባቸው አይመስለኝም፡፡ ከፊት መሆን እና ኃላፊነት መውሰድ አለባቸው፡፡ ቁርጠኛ መሆን አለባቸው፡፡ ይኼ የባንዲራ ጉዳይ በፓርላማ ደረጃ መወሰን ያለበት ይመስለኛል፡፡ እንጂ በሕዝብ ይሁንታ ተብሎ ወደውጪ መገፋት ያለበት አይመስለኝም ፡፡ በአጭሩ፤ በሕዝብ ይሁንታ የሚለው የኢዜማ እሳቤ ለኔ ግልፅ አይደለም፡፡

*ኢዜማ የፖለቲካ ልሂቁን እንጂ የሰፊውን ሕዝብ ቀልብ የሚስብ ፓርቲ አይደለም ይላሉ፤ ፕሮግራሙ ግን ለታችኛው ወገኖች የተሻለ ነው ይላሉ፡፡ አንተ በዚህ አስተያየት ትስማማለህ?*

ምን ማለት ነው? ሀሳቡ እርስ በርሱ የተምታታ እኮ ነው፡፡ የፖለቲካ ልሂቁን እንጂ የሰፊውን ሕዝብ ቀልብ የሚስብ ፓርቲ አይደለም ከተባለ ድምዳሜ ላይ ተደርሷል እኮ፡፡ የልሂቃን ነው ተብሏል፡፡ አበቃ ፡ ፡ የልሂቃን ነው ካሉ በኋላ፣ ፕሮግራሙ ግን ለታችኛው ወገኖች የተሻለ ነው ማለት ማምታታት ነው፡፡ ይህንን የሚሉ ሰዎች ግራ ተጋብተዋል፤ ግራ መጋባት ብቻ አይደለም ተምታቶባቸዋል፡፡

የሆነ ሆኖ የኢዜማ ፕሮግራም ልሂቃኑንም ታችኛውንም ወገን ሊያሰባስብ የሚችል ነው ለማለት የፈለጉ ይመስለኛል ፡፡ እኔ እንደዛ ሀሳቡን ብረዳላቸው ይሻላል ፡፡ እንደዚያ ከሆነ ልክ ናቸው፡፡ ሁሉንም ወገን ሊያስማማ የሚችል ፕሮግራም ነው ብዬ አምናለሁ፡፡ የቀረው የማስረዳት፣ የማብራራት፣ የመተንተን ወ.ዘተ... ጉዳይ የፓርቲው አባላት ጉዳይ ይመስለኛል፡፡

*ኢዜማን ከዚህ በፊት ከነበሩት ተፎካካሪ ፓርቲዎች እና አሁን ካሉት አንፃር እንዴት ትገመግመዋለህ?*

ኢህአዴግ የሀገሪቱን መንበረ ስልጣን ከተቆጣጠረ ወዲህ በተቃዋሚ ፓርቲ ረገድ ዕድለኛ አይደለንም፤ ወይም ዕድለኛ አልነበርንም ማለት ይቻላል ፡፡ ለዚህ ደግሞ ሁለት ምክንያቶች ያሉ ይመስለኛል ፡፡ አንደኛው ምክንያት ሀገሪቱን ይመራ የነበረው ወገን የይስሙላ እንጂ እውነተኛ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት እንዲኖር የማይፈልግ ስለነበር ነው፡፡ ይህንንም ለማድረግ ይቻለው ዘንድ ጠንከር ያሉ ፓርቲዎችን አናት አናታቸውን እየወቀረ ሲያስበረግጋቸው፣ ሲያዋክባቸውና ሲያሳድዳቸው ነው የኖረው፡፡

ሁለተኛው ምክንያት በሕዝብ ስም፣ በዴሞክራሲ ሥም፣ በፓርቲ ስም ተደራጅተው ይነግዱ የነበሩ ‹‹የፖለቲካ ኃይሎች›› እንደ አሸን መፍላታቸው ነው ፡፡ እንደ አሸን መፍላት ብቻ ሳይሆን ለኢህአዴግ አሻጥር ተመቻችተው ሕዝብን ለአፈና አሳልፈው የሰጡ ነበሩ፡፡

ኢዜማን ከእነዚህ ‹‹ፓርቲ››ዎች ጋር ማነፃፀር አስቸጋሪ ይመስለኛል፡፡ ምክንያቱም ባለፉት ሁለት ሶስት ዓመት ካደረገው እንቅስቃሴ አንፃር በዕውቀትና በብስለት የሚራመድ ፓርቲ መሆኑን ነው የተረዳሁት፡፡ ዓላማ እና ዒላማ ያለው ድርጅት ይመስለኛል፡፡ ከሚያደርገው እንቅስቃሴ አንፃር ከየት ተነስቶ የት ለመድረስ አስቀድሞ ያሰላ፣ እርምጃውንም ጠንቅቆ የሚያውቅ ይመስለኛል፡፡ የኢዜማ ጉዞ በይመስለኛል ብቻ የታጠረ አይደለም፤ ሕዝብን እና ሃገሪቱን ከየት ወዴት መውሰድ እንደሚፈልግ ያሰላ፣ ማስላት ብቻ ሳይሆን በጥናት በተረጋገጠ መልኩ መዳረሻውን ማመላከት የቻለ ድርጅት ነው ብዬ አምናለሁ፡፡

ለዚህ ደግሞ አብነቱ ሁሉንም የሕብረተሰብ ክፍል በየደረጃው ተጠቃሚ የሚያደርግ የምጣኔ ሀብት ዕድገትና ልማት ለማምጣት ይረዳሉ፤ ማኅበራዊ ፍትህ ያሰፍናሉ፤ ሰላም ያረጋግጣሉ፤ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓተ-መንግሥትን በኢትዮጵያ ዕውን ያደርጋሉ ያላቸውን ከ20 በላይ የፖሊሲ ሰነዶች መቅረፅ እና የሚመለከታቸውን ማወያየት መቻሉን መጥቀስ ይቻላል፡፡ የኢዜማ የፖሊሲ ጥናት ሰነዶች ከዚህም በላይ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ እኔ በግርድፉ የማውቃቸውን ነው የነገርኩህ፡፡ እነዚህን የፖሊሲ ሰነዶች ምን ያህሉን ሕዝቡ ያውቃቸዋል? አላውቅም፡፡ ኢዜማ እነዚህን ሰነዶች ለሕዝብ እንዲዳረስ፣ ወይም ሕዝብ እንዲያውቃቸው አድርጓል ወይ? አላውቅም ፡፡

እንዲያም ሆኖ ግን በብስለት፣ በስሌት እና በዕውቀት እየተራመደ ያለ ድርጅት ኢዜማ ብቻ ይመስለኛል፡፡ ሌሎቹ ፓርቲ መሆናቸውን እንጂ በዚህ መንገድ የነጠረ ሥራዎች የሰሩ መሆናቸውን አላውቅም፡፡ አማራጭ አለን ሲሉ እንጂ አማራጫቸውን ለራሳቸው ፓርቲ አባላት እንኳ ሲያቀርቡ በዜና ደረጃ እንኳ አልሰማሁም፡፡ ስለዚህ ለጊዜው የተሻለ የምለው ፓርቲ ኢዜማን ነው፡፡

*በሚቀጥለው ምርጫ ድምፅ ትሰጣለህ? ከሰጠህ ለማን በምን መስፈርት?*

(ሳቅ) አዎ እመርጣለሁ፤ ድምፄን ድምፅ ለሚሆነኝ ፓርቲ እሰጣለሁ፡፡ መስፈርቴን እና ድምፄን ለማን እንደምሰጥ ግን አልነግርህም፡፡ .... ምናልባትም በምርጫ ክርክር ወቅት መስፈርቴን የሚያሟላ፣ ከመስፈርቴም በላይ ሚዛን የሚደፋ ተወዳዳሪ ሊመጣ ይችላልና፡፡

*ኢዜማ የሚያራምደው የዜግነት ፖለቲካ አሁን ላለው የብሔር ፖለቲካ ከፍተኛ ተግዳሮት ይሆናል ተብሎ ይታሰባል፡፡ ኢዜማ ይሄን አስተሳሰብ ሰብሮ የመውጣት ዕድል አለው?*

ከአግላይ ወደ አሳታፊ ሥርዓት መሸጋገር ቀላል አይደለም፤ ሽግግሩ እጅግ ፈታኝ መሆኑ የማይታበል ሐቅ ነው፡፡ ኢትዮጵያችን ላለፉት 30 ዓመታት በአግላይ ሥርዓት ተቀፍድዳ ነው የኖረችው፡፡ ለዚህ ዕውነት ደግሞ እማኝ ማቅረብ አያስፈልግም ፡፡ ሰዎች ሥልጣን የሚያገኙት፣ መሬት የሚሰጣቸው፣ የሚደራጁት፣ የባንክ ብድር ወ.ዘተ የሚሰጣቸው በዕውቀታቸው፣ በብቃታቸው፣ በችሎታቸው፣ በክህሎታቸው አልነበረም፡፡ በዘራቸው ምክንያት ነበር፡፡ ▶



አግላይ ሥርዓት እንዲህ ነው፤ ሰው ከሰውነት ይነጥላል፡፡ መስፈርቱ፣ ዘር ወይም ሌላ ተመሳሳይነት ይሆናል፡፡ ሕወሓት/ ኢሕአዴግ አግላይ የፖለቲካ ሥርዓት ገንብቶ፣ አግላይ የኢኮኖሚ ሥርዓትን አንሰራፍቶ፣ ጥቂቶች እንዳሻቸው እየተዘባነኑ እንዲኖሩ ነው ያደረገው፡፡ ይህም ብቻ አይደለም ከእነሱ ስር ተኮልኩለው የጥቅም ፍርፋሪ ሲለቅሙ የነበሩ ኃይሎች ነው ያፈራው፡፡

አሁን ብልፅግና ፓርቲ ለውጥ ለውጥ እያለ ነው፤ ያንን ‹‹መስመር›› አልከተልም ፤ ፍልስፍናዬ ‹‹መደመር›› ነው ብሏል፡፡ ለምን መሰለህ? ያ አግላይ ሥርዓት እንደማያዋጣው ገብቶታል፡፡ እንዲያም ሆኖ ብልፅግና ሀገር ማረጋጋት እንኳ አልተሳካለትም፡፡ ለምን መሰለህ? በማንኛውም ዘመን እና ጊዜ ለውጥን ማምጣት አስቸጋሪ የሚሆነው ከውጪ በሚገጥመው ተግዳሮት ባለመሆኑ ነው፤ ተግዳሮቱ የሚገጥመው ከውስጥ ነው፤ ከውስጥ ያንን አሮጌ አስተሳሰብ የተሸከሙ ናቸው እንቅፋት የሚሆኑት፡፡ አንድ እግራቸውን እዚያ፣ አንድ እግራቸውን እዚህ አንፈራግጠው ስለሚገኙ ማለት ነው ፡፡ በዚያ አግላይ ሥርዓት ተጠቃሚ ነበሩ፤ ለውጥ ከመጣ ያንን ጥቅም እናመጣለን ብለው ይሰጋሉ፡፡ በቀላሉ የማይሞተው አሮጌ አስተሳሰብ ተሸካሚዎች ናቸው ዋነኞቹ የለውጥ እንቅፋቶች፡፡

ልክ እንደዚያው ሁሉ ከአግላይ የዘረኝነት መንፈስ መውጣት እና በዜግነት ላይ ወደ ተመሰረተ አስተሳሰብ መግባት ቀላል አይደለም፡፡ ከባድ ነው፤ ትግሉም ፈታኝ ነው፡፡ ምክንያቱም ከ30 ዓመት በላይ ሲገነባ የኖረ የዘረኝነት መንፈስ በቀላሉ የሚፈርስ/ የሚለወጥ አይደለም፡፡ በዚያ የዘር አደረጃጀት ውስጥ ሥልጣን የተቆናጠጠ፣ ሀብት ያፈራ፣ ከሕግ በላይ ሆኖ የኖረ ኃይል ወዘተ ...ዛሬ በሕግ እና በእኩልነት እሳቤ ትመራለህ ብትለው በቀላሉ አይቀበልህም፡፡ ይህም ብቻ አይደለም፤ ነገ በዚያው የዘረኝነት መንገድ ተደራጅቶ፣ ሥልጣን ይዞ፣ መዝረፍ፣ ማስዘረፍ የሚፈልግ፣ ዕድሜ ዘመኑን ሁሉ በዘረፋ ሲቀና የኖረ ኃይል አለ፡፡ እነዚህን ኃይሎች መግራት፣ እና መርታት ቀላል አይደለም፤ ከባድ ትግል ይጠይቃል፡፡

አሁን የኢትዮጵያ ሕዝብ ‹‹ከጉዳት›› ተምሯል፤ እየተማረም ነው፡፡ ከነዚህ አግላይ ኃይሎች የተረፈው፤ እንግልት፣ ስደት እና ሞት ነው፡፡ ከዚህ ባሻገር ግን እንደ ኢዜማ ያሉ የዜግነት ፖለቲካን የሚያራምዱ ኃይሎች ትግል ይሻል፡፡ በማስረዳት፤ ነገሮችን በመተንተን፣ በማስተማር .... ወዘተ የዘረኝነትን አስተሳሰብ መስበር ያስፈልጋል፤ ደግሞም የጊዜ ጉዳይ እንጂ እሳቤውን መስበር ይቻላል፡፡

**‹‹ ... በማንኛውም ዘመን እና ጊዜ ለውጥን ማምጣት አስቸጋሪ የሚሆነው ከውጪ በሚገጥመው ተግዳሮት ባለመሆኑ ነው፤ ተግዳሮቱ የሚገጥመው ከውስጥ ነው፤ ከውስጥ ያንን አሮጌ አስተሳሰብ የተሸከሙ ናቸው እንቅፋት የሚሆኑት ፡፡ አንድ እግራቸውን እዚያ፣ አንድ እግራቸውን እዚህ አንፈራግጠው ስለሚገኙ ማለት ነው ፡፡››**

*የኢዜማ ድክመት ነው፤ ሊያሻሽል ይገባዋል የምትለው ነገር አለ?*

ኢዜማ እየሠራ ያለ ድርጅት ነው፤ ነገር ግን የሚሠራውን ለራሱ ብቻ እያወራ ያለ ድርጅት ይመስለኛል፡፡ ምን ማለት ፈልጌ ነው? ከላይ እንደነገርኩህ በርካታ ፖሊሲዎችን ሰነዶችን አዘጋጅቷል፡፡ እነዚህን ሥራዎቹ በቅርበት የሚያውቁት ወይም የምናውቀው ግን ጥቂቶች ነን፤ ለዚያውም በሥራ ምክንያት ነው የምናውቀው፡፡ ኢዜማ ሥራዎቹን የማስተዋወቅ ሕዝብ ውስጥ የማስረፅ ችግር አለበት ማለት ነው፡፡ ይህ ድክመት ይመስለኛል፡፡

ሌላው የኢዜማ ድክመት የሚመስለኝ አንዳንድ ጉዳዮች ላይ ምላሽ ከመስጠት መዘግየት ይመስለኛል፡፡ እርግጥ ነው የፓርቲው ሰዎች ‹‹እኛ ሕዝብን ስሜታዊ በሚያደርጉ ነገሮች ላይ መግለጫ ወይም ምላሽ ለመስጠት አንሮጥም፤ ሥራ ላይ ነን›› ሲሉ ሰምቻለሁ፡፡ ልክ ናቸው፤ በሆነ ባልሆነው ምላሽ መስጠት አግባብ ላይሆን ይችላል ፡፡ ነገር ግን የድርጅቱን ድርጅትነት ወይም የፓርቲውን ፓርቲነት የሚመስክሩ የሃሳብ ማዕዘናት ላይ ምላሽ ከመስጠት፣ አቋምን ከመግለፅ መዘግየት ያለበት አይመስለኝም፡፡ ለምሳሌ በነፃ ተቋማት ግንባታ ላይ ያለውን የማያወላውል አቋም እንዳለው ካለጊዜ ገደብ መግለፅ አለበት ብዬ አምናለሁ፡፡ ነፃ ተቋማት ከምንላቸው መሀል አንዱ ደግሞ ፍ/ቤት ነው፡፡ ፍ/ቤቶች ከአንድም፣ አራት አምስቴ የሰዎችን መብት በአደባባይ ሲጥሱ፣ የኢዜማ የበዛ ዝምታ ትክክል አይመስለኝም ፡፡ ይህንን በፅኑ ዓላማዎቹ ላይ ወቅታዊ ምላሽ አለመስጠት ድክመት ያርማል ብዬ አምናለሁ፡፡

*እኔ ጨርሻለሁ የምትጨምርልኝ ነገር ካለ .......*

በሴቶች ተሳትፎ ረገድ ኢዜማ የያዘው አቋም የሚደነቅ ነው፡፡ እሱን ሳላደንቅ አላልፍም፡፡ ወጣት ሴቶችን ወደፊት እያመጣ ነው፡፡ ሴቶችን ብቻ ሳይሆን ወንዶችንም ወደፊት እያመጣ ነው፡፡ ጥሩ ነው፡፡ እነዚህን ወጣቶች፤ እነዚህን አዳዲስ ፊቶች ግን የማስተዋወቅ፣ ከሕዝብ ጋር የማገናኘት የተግባቦት ስልት መንደፍ ያለበት ይመስለኛል፡፡ ፓርቲው የተሰፈኞች፣ የነገዋ ኢትዮጵያን የሚመሩ ወጣቶችም መሆኑን የማሳወቅ ግዴታ አለበት፤ ይህንን የተለያየ መድረክ በማዘጋጀት መከወን አለበት፡፡ የግድ ደረቅ የፖለቲካ መድረክ ማዘጋጀት ላይሆን ይችላል፡፡ የሥነ ፅሁፍ፣ የስፖርት መድረክ .... ወዘተ በማዘጋጀት ወጣቶቹ መሪዎች አጭር ግን አነቃቂ ንግግር እንዲያደርጉ በመጋበዝ ሊሆን ይችላል፡፡ ይህንን ነው መጨመር የምፈልገው፡፡

*ለቆይታችን በጣም አመሰግናለሁ፡፡*

እኔም አመሰግናለሁ፡፡

# ነፃ ሀሳብ

ማሳሰቢያ፡- ይህ ፅሁፍ የፀሐፊውን አቋም ብቻ ነው የሚወክለው!
የዚህ ፅሁፍ አዘጋጅን ማግኘት ቢያስፈልግ mesaytbt@gmail.com ይጠቀሙ

## ትኩረት የተነፈጋቸው የሥነ - ሕዝብ ጉዳዮች

መሳይ ግርማ



የሥነ-ሕዝብ ፖሊሲ (Population Policy) በተለምዶ እንደሚገለፀው የሥነ-ሕዝብ አወቃቀር ሂደቶች በተለይም የውልደት፣ የሞት እና ፍልሰት ላይ ተፅእኖ ለማምጣት ዓላማ ያደረገ እርምጃ ነው። ሥነ-ሕዝብ የአንድ ሀገር ሁለንተናዊ ደህንነት እና እድገት ውስጥ ጉልህ ሚና እንዳለው ዘርፍ በጠንካራ ፖሊሲ ማእቀፍ ውስጥ ሊተገበር እንደሚገባ ባለሙያዎች ይጠቅሳሉ።

በአገሪቱ ውስጥ የሥነ-ሕዝብ ዋነኛው የመረጃ ምንጭ በ1976 ዓ.ም፣ 1986 ዓ.ም እና 1999 ዓ.ም የተካሄዱት የሕዝብ እና ቤት ቆጠራዎች ናቸው። በ2005 ዓ.ም የተካሄደው የውስጠ-ቆጠራ ግምቶች (ICPS) የሕዝብ ብዛት እና እድገት መረጃን ሰብስቦ ነበር። ሆኖም ግን በጥናቱ ውስጥ ያሉት ውጤቶች ናሙና ላይ በመመርኮዝ የተገኙ ግምቶች ሲሆኑ ተጓዳኝ የናሙና ግድፈቶች አለባቸው። በተጨማሪም የውልደት፣ የሕፃናት ሞት እና የቤተሰብ ዕቅዶች ተቀባይነት፣ ለውጥ እና አዲስ ግንዛቤዎችን ለማወቅ 1993 ዓ.ም ፤ 1998 ዓ.ም፣ 2004 ዓ.ም እና 2012 ዓ.ም አራት የሥነ-ሕዝብ እና የጤና ጥናት ተካሄዷል።

የሕዝብ ቆጠራ እና ጥናት ውጤት በአንድ የተወሰነ ወቅት ላይ የሕዝቡን ብዛት እና እድገት ለማወቅ ወይም ለመገመት ይጠቅማሉ። የሥነ-ሕዝብ ትንበያ ለልማት እቅድ ለመቅረጽ አስፈላጊ ናቸው፡፡ ልደት፣ ሞት እና ስደት ሥነ-ሕዝብ ላይ ተጽዕኖ ስላላቸው የወደፊቱን ለመተንበይ በእነዚያ መለኪያዎች ላይ መረጃ ያስፈልጋል።

በኢትዮጵያ በቂ የሆነ መረጃ አለመኖር፣ የመረጃ ጥራት ችግር፣ በመረጃ አሰባሰብ ውስጥ ወጥነት አለመኖር /መዛባት/ የመለኪያ ስህተቶች፣ የመረጃ እጥረት፣ ጊዜውን ያልዋጀ መረጃ መኖር፣ የመሰብሰብ ቀጣይነት አለመኖር፣ በመሰብሰብ እና በማሰራጨት መካከል የጊዜ መዘግየት፣ የወሊድ እና የሟች መጠን ለውጥ ላይ የተደረጉ ጥናት እና ምርምር በቂ አለመሆን እንዲሁም ቁጥሮቹን የሚቀያየሩ ብዙ ምክንያቶች መኖር የሥነ-ሕዝብ ትንበያዎችን በእጅጉ ያከብዳቸዋል፡፡

የማዕከላዊ ስታትስቲክስ ኤጀንሲ መረጃ እንደሚያመለክተው፣ በ1963 ዓ.ም የኢትዮጵያ የሕዝብ ብዛት በግምት 28.4 ሚሊዮን እና በየዓመቱ 2.65 በመቶ ያድግ ነበር። በቋሚነት የኢትዮጵያ ሕዝብ ላለፉት አራት አስርተ ዓመታት ያለማቋረጥ አድጓል። የሕዝብ ቁጥሩም የመጀመሪያው የሕዝብ ቆጠራ በተደረገበት በ1976 39 ሚሊዮን፤ ሁለተኛው የሕዝብ ቆጠራ በተደረገበት በ1986ዓ.ም 53.5 ሚሊዮን እና ሶስተኛ የሕዝብ ቆጠራ በተደረገበት በ1999 ዓ.ም 73.8 ሚሊዮን ነበር።

ኢትዮጵያ ልክ እንደ አብዛኞቹ ከሰሃራ በታች ያሉ የአፍሪካ ሀገራት የሕዝብ ቁጥር ከፍተኛ ዕድገት ያሳየችው ባለፈው ምዕተ ዓመት መገባደጃ ላይ ነበር። ከ1973-1978 ዓ.ም የኢትዮጵያ ሕዝብ ብዛት በዓመት 2.92 በመቶ ነበር እድገት ያሳየው፡፡ ይህ አሀዝ ከ1983-88 ባሉት 5 ዓመታት 3.5 በመቶ አድጓል። ኢትዮጵያ ላለፉት 20 ዓመታት የሕዝቧን ዕድገት መጠን (Population Growth Rate) መቀነስ ችላለች። የሕዝብ ቁጥር ዕድገቱ በ1988 ዓ.ም ከነበረበት 3.5 በመቶ በ2003-08 ዓ.ም ወደ 2.5 በመቶ ዝቅ ያለ ሲሆን አሁን ያለው የወሊድ እና ሞት አዝማሚያዎች ያለ ምንም ጣልቃ ገብነት ከቀጠሉ የኢትዮጵያ ሕዝብ ብዛት እድገት በ2018-23 ዓ.ም ወደ 2.2 በመቶ በመቀጠል በ2023-28 ዓ.ም ወደ 1.8 በመቶ ዝቅ እንደሚል ይገመታል።

የ2012 ዓ.ም መባቻ የተ.መ.ድ (የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት) የዓለም አቀፋዊ መረጃ ላይ በመመርኮዝ አሁን ያለው የኢትዮጵያ ሕዝብ 115.2 ሚሊዮን ሲደርስ እድገት መጠኑም በዓመት 2.66 በመቶ ነበር። በዚሁ ዓመት ኢትዮጵያ ከዓለም ሕዝብ ብዛት 1.47 በመቶ ድርሻ ስትወስድ፤ በሕዝብ ቁጥር ከዓለም ሀገራት 12ኛ ደረጃን ትይዛለች። በተ.መ.ድ የሕዝብ ብዛት እና እድገት ትንበያ መሰረት ኢትዮጵያ አሁን ያለውን የሕዝብ ቁጥር እድገት ደረጃዋን ያለምንም ጣልቃ ገብነት የምትቀጥል ከሆነ ሕዝቡ በሚቀጥሉት 40 ዓመታት በእጥፍ በመጨመር በ2053 ዓ.ም 232 ሚሊዮን ይደርሳል፡፡
ከሕዝብ ብዛት እና እድገት መለኪያዎች በተጨማሪም በ2012 ዓ.ም የተ.መ.ድ የዓለም አቀፋዊ መረጃ እንደሚያመለክተው የኢትዮጵያ፡-

- መካከለኛ (አማካይ) ዕድሜ 19.5 ዓመታት፤
- ከ15 ዓመት በታች የሆነው ሕዝብ 43.5 ከመቶ ድርሻ ይወስዳል፤
- 2.5 ሚሊዮን አዲስ ወጣት የሥራ እድሜ ላይ ደርሰዋል፤
- 24 ከመቶ የሚሆኑት የሕዝቡ ክፍል የመውለድ ዕድሜ ላይ ያሉ ሴቶች ነበሩ፤
- የአንድ ዜጋ አማካይ የሕይወት ዘመን ለሁለቱም ጾታዎች 65.97 ዓመት፤ ለወንድ 64.09 ዓመት ለሴቶች ደግሞ 67.88 ፤ እንዲሁም
- አማካይ የሕዝብ ጥቅጥቅነት (Population Density) 115 ሰዎች በ 1 ካ.ሬ ኪ.ሜ. ነበር።

በኢኮኖሚ መሸከም አቅም ዝቅተኛ ከሚባሉት ሀገራት ተርታ የምትመደበው ሀገራችን እንደዚህ ▶



▶ በከፍተኛ ደረጃ እየጨመረ ላለው የሕዝብ ቁጥር የመሠረታዊ ፍላጎት ማሟላት እጅግ አዳጋች ይሆንባታል፡፡ ኢትዮጵያን እያስተዳደረ ያለው መንግሥት ብዛት ያላቸው የማኅበራዊ፣ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ይዘታ ያላቸው እቅዶች እና ሃሳቦች ነድፏል፤ ተግብሯልም። ቢሆንም ግን አብዛኞቹ ትግበራ፣ አፈጻጸም እና ክትትል ላይ በሚታዩ ድክመት እና የሥነ-ሕዝብ ጉዳይን እምብዛም ከግምት ባለማስገባት ሀገሪቱን ለብዙ ችግሮች እና እዳዎች ጥለዋታል። የአንድ ሀገር ሕዝብ ለሀገር እድገት እና ተስፋ ጥቅም ቢኖረውም ሀገሪቱ ካላት የኢኮኖሚ ደረጃ፤ የቆዳ ስፋት እንዲሁም አላቂ እና ቋሚ የተፈጥሮ ሃብት አኳያ አብሮ መጓዝ ካልቻለ ከጥቅሙ ይልቅ ጉዳቱ ያመዝናል። በዚህም ላይ እንደ ኢትዮጵያ ላሉ የምግብ እጥረት እና የከፋ ድህነት ላለባቸዉ ሀገራት የማኅበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ እቅድ ሲነድፍ ያለውን ሕዝብ ብቻ ሳይሆን ወደፊት ለሚጨመረዉ ሕዝብ ታሳቢ መደረግ አለበት።

ኢትዮጵያ እንደ አገር ያላትን የኢኮኖሚ ደረጃ፣ የቆዳ ስፋት፣ አላቂ እና ቋሚ የተፈጥሮ ሃብት እንዲሁም የመሬት ምርታማነትን መቀነስን ማእከል አድርጋ ለዜጎች ህይወት መሻሻል የምታደርገው ጉዞ ያለ ጠንካራ የሥነ-ሕዝብ ፖሊሲ የሚታሰብ አይደለም። ሳይንሳዊ ጥናቶች እንደሚያሳዩት የአንድ ሀገር ከኢኮኖሚ ደረጃ ጋር ያልተመጣጠነ ፈጣን የሕዝብ ዕድገት ለተለያዩ ችግሮች ይዳርጋል።

ፈጣን የሕዝብ ዕድገት ለማኅበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እንዲሁም ለተፈጥሮ ሀብት ችግሮች ይዳርጋል፡፡ የኢኮኖሚ ጥንካሬ መዳከም፣ የነፍስ ወከፍ ገቢ መቀነስ፣ የቁጠባ መጠን መቀነስ፣ የአየር ንብረት መለወጥና የአካባቢ መበከል፣ የተፈጥሮ ሀብት መራቆት፣ የቆሻሻ ክምችት መጨመር፣ የአኗኗር ሁኔታ መዛባትና የኑሮ ውድነት መጨመር፣ ሥራ-አጥነት መብዛት፣ ረሃብ እና የማኅበራዊ መስተጋብር መዛባትና ማኅበራዊ ችግሮች (ወንጀል፣ ዝሙት አዳሪነት፣ ስርቆት፣ ዝርፊያ፣ ግጭት፣ ጦርነት፣ እርስ በርስ ግጭት፣ ድርቅ እና ረሃብ) መበራከት ከብዙ በጥቂቱ የሚነሱ ችግሮች ናቸው። ባለፉት ዓመታት እነዚህ ችግሮች በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ በሀገራችን ተከስተዋል፡፡ ትኩረት ካልተሰጣቸው ወደፊትም እየተባባሱ መሄዳቸው አይቀሬ ይሆናል፡፡

### የኢትዮጵያ የሥነ-ሕዝብ ፖሊሲ ተሞክሮ

በ1985 ዓ.ም የኢትዮጵያ መንግሥት ለመጀመሪያ ጊዜ ግልፅ፣ አጠቃላይ እና ዘርፈ ብዙ የሆነ ያለውን የሥነ-ሕዝብ ፖሊሲን ቀረጸ፡፡ ፖሊሲው ሀገሪቷ ለአስርተ ዓመታት በፖለቲካው ቀውስ ፣በአየር ሁኔታ መዛባት፣ የኢኮኖሚ ምጣኔ ችግር እና የምርታማነት መዳከም ውስጥ ስላሳለፈች አብዛኛው ሕዝብ በሁለገብ ድህነት ዉስጥ እንዲቆይ ማድረጉን አስረድቷል፡፡ ለዚህም ደግሞ ማሳያ የጥቅል ምርተ-አገር ዕድገት መጠን ከሕዝቡ እድገት መጠን በጣም ዝቅተኛ እንደነበር ጠቅሷል፡፡ (በ1983 ዓ.ም የጥቅል ምርተ-አገር ዕድገት 1.9 በመቶ የሕዝቡ እድገት መጠን ደግሞ 3.2 በመቶ ነበር) በዚህም የተነሳ ሕዝቡ ለምግብ ዋስትና እጦት እና ለተደጋጋሚ ረሃብ ፤ ለሥራ አጥነት እና ለጤንነት መጓደል ተዳርጓል። ፖሊሲው የሕዝቡን ዕድገት መጠን ከኢኮኖሚው ጋር በማጣጣም እና የአገሪቱን ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ልማት ዘላቂ ለማድረግ ያለመ ነበር፡፡ የሥነ-ሕዝብ ፖሊሲው ሲጽድቅ የአገሪቱ አጠቃላይ ሕዝብ ብዛት 53.3 ሚሊዮን አካባቢ ይገመታል፡፡

የሥነ-ሕዝብ ፖሊሲው ከጸደቀ በኋላበርካታየሥነ-ሕዝብዘርፎችላይአተኩሮ የተለያዩ ፕሮግራሞች ተቀርፀዋል። በዚህም የተነሳ አገሪቱ የሥነ-ሕዝብ ትምህርትና የጤና አገልግሎቶችን፣ የሥርዓተ-ፆታ ፍትሃዊነትን፣ እኩልነቷን እና ሴቶችን የማጎልበት እና የሴቶች ብልፅግናን በማስፋፋት ረገድ የተወሰነ መሻሻል አሳይታለች። ሆኖም ብዙ ጥናቶች እንደሚያመለክቱት ፖሊሲው 1986 ዓ.ም እስከ 1996 ዓ.ም ተቋማዊ መዋቅሮችን ለመፍጠር እና ፖሊሲውን ለመተግበር የተሠሩ ጥረቶች ነበሩ። ከ1996 ዓ.ም በኋላ ግን የሥነ-ሕዝብ ፖሊሲዉን ለመተግበር የፖለቲካ ቁርጠኝነት አለመኖር እና የአመራር እጥረት በመኖሩ በ2008 ዓ.ም እስከሚያበቃ ድረስ በአግባቡ አልተተገበረም። ለዚህ ደሞ ዋነኛ ምክንያት በወቅቱ የነበሩ የከፍተኛ-ደረጃ የመንግሥት አመራሮች ኢትዮጵያ በዓለም አቀፍ ተቋማት እና ሀገራት ግፊት ተገፍታ ነው እንጂ የሥነ-ሕዝብ ጉዳይ የአገሪቱ ችግር አልነበረም ብለው ማመናቸው ነበር።

ከመንግሥት የፖለቲካ ቁርጠኝነት ማጣት በተጨማሪ ፖሊሲው ውጤት እንዳያመጣ እንቅፋት የሚሆኑ በርካታ ነባር እና ቀጣይ ችግሮች አሉ፡፡ እነዚህም ችግሮች በፖሊሲ ክፍተቶች እና የአፈፃፀም ችግር ምክንያት የተከሰቱ ናቸዉ።

ዋና ዋና የፖሊስ ክፍተቶች መካከል ለሥነ ሕዝብ ፓሊሲው የዕድሜ መዋቅር ለውጥ እና የሕዝብ ቁጥር (ሥነ-ሕዝባዊ ትሩፋት) በከፍተኛ እና አሳሳቢ ደረጃ ላይ ማደጉን ከእሳቤ አለመውሰድ፤ ጠንካራ የሕግ መሠረት አለመኖር ፤ ፖሊሲው ሲቀረፅ አሳታፊ ያልነበረ መሆኑ ፤ የማኅበራዊ-ኢኮኖሚያዊ የልማት ዕቅድ ከሥነ-ሕዝብ ዕቅድ እና መለኪያዎች ጋር አለማጣጣም፤ በፓሊሲው ዉስጥ ያልተካተቱ ወይም ተገቢ ትኩረት ያልተሰጣቸው ጉዳዮች መኖር፤ የፖሊሲ ዓላማዎች የሚለኩ አለመሆን እና የክትትልና ግምገማ ማዕቀፍ አለመኖር የሚጠቀሱ ናቸው።

ዋና ዋና የፖሊስ አፈፃፀም ችግር የታየባቸው መካካል ደግሞ ብሔራዊ የሥነ-ሕዝብ ምክር ቤት ማቋቋም አለመቻል፤ ምንም አይነት አጠቃላይ የሥነ-ሕዝብ ፕሮግራም አለመቀረጽ እና አለመተግበር፤ ለሥነ-ሕዝብ ፓሊሲ ማስፈፀሚያ በቂ የሆነ በጀት አለማዘጋጀት፤ ትግበራው እስከ ትንሹ የአስተዳደር ክፍሎች ድረስ አለመውረድ፤ የሥነ-ሕዝብ ጉዳይ ፖለቲካዊ አንድምታው እንዲጎላ መደረጉ፤ ውስን የሆነ የመረጃ፣ የትምህርትና የግንኙነት ሁኔታ መፈጠሩ እና የቀጠሉ ባህላዊ ልምዶች፣ እምነቶች እና አመለካከቶችን መጥቀስ ይቻላል።

### ማጠቃለያ

-ሥነ-ሕዝብ በማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ጉዳዮች ላይ የሚያስከትለውን ጉዳት በቂ ትኩረት ባለመሰጠቱ በሀገራችን ከፍተኛ የሆነ የኢኮኖሚ አለመመጣጠንና የማኅበራዊ ፍትህ መጓደል አምጥቷል፡፡ ብዛት ያለው ከድህነት ወለል በታች የሆነ ዜጋ እንዲኖርና መካከለኛ ገቢ ያለው ዜጋ ቁጥር እምብዛም እንዲሆን አድርጓል፡፡ በጣም ጥቂት ከፍተኛ የኑሮ ደረጃ ላይ ያሉ ዜጎች የሀገሪቱን ሀብት ሙሉ ለሙሉ በሚያስብል ደረጃ ተቆጣጥረውታል፡፡ ስለሆነም የሥነ-ሕዝብ ጉዳይ እና ተያያዥ ዘርፎቹ ወደፊት ትኩረት ከሚሹ እና አሁን ላይ በሚያሳስብ ደረጃ ከተዘነጉት ጉዳዮች መካከል ዋነኛው መሆኑን ልብ በማለት የሥነ-ሕዝብ ፖሊሲ ማዘጋጀት ለነገ የማይባል ቀዳሚ ሥራ መሆን አለበት፡፡

# ‹‹ምርጫ 2013ትን እንደማንኛውም ምርጫ አንመለከተውም››

## ከውሰር እድሪስ የኢዜማ ምርጫ ስትራቴጂና ማኔጅመንት ኮሚቴ ጽህፈት ቤት ኃላፊ

ጥር 12 ቀን 2013 ዓ.ም (የዜጎች መድረክ)



የኢትዮጵያ ዜጎች ለማኅበራዊ ፍትህ (ኢዜማ) የምርጫ ስትራቴጂና ማኔጅመንት ኮሚቴ ጽህፈት ቤት ኃላፊ የሆኑት ከውሰር እድሪስ ፓርቲያቸው የምርጫ ዝግጅቱን አጠናቆ ወደ ምርጫ ዘመቻ ለመግባት ዝግጅቱን በማጠናቀቅ ላይ እንደሚገኝ ተናገሩ፡፡ ከምርጫ ጋር በተያያዙ ጉዳዮች ላይ ጥር 06 ቀን 2013 ዓ.ም ከአሀዱ ሬዲዮ ጋር ቆይታ ያደረጉት ኃላፊዋ፣ ኢዜማ የምርጫ ዝግጅቱን አጠናቆ ወደ ምርጫ ዘመቻ ለመግባት አንድ ወር እንደቀረው ተናግረዋል፡፡ የፓርቲያቸው የምርጫ ዘመቻ ሶስት ደረጃዎች እንዳሉት የጠቆሙት ኃላፊዋ፣ በብሔራዊ፣ በክልልና በምርጫ ወረዳ ደረጃ ዘመቻው እንደሚካሄድ ገልጸዋል፡፡

ሶስቱ የዘመቻ ቡድኖች የሕዝቡን ችግር በማጥናት ተግባራዊ ሊሆን የሚችል መፍትሄዎች እንደሚያስቀምጡ ያስረዱት ኃላፊዋ፣ በአካባቢያቸው ተቀባይነት ያላቸውና አቅም ያላቸው እጩዎችን እንደሚያዘጋጁና ለምርጫው ዝግጅት የሚረዳቸውን ግብአትና ሀብት እንደሚያሰባስቡ ጠቁመዋል፡፡

ምርጫ 2013ትን እንደማንኛውም ምርጫ ፓርቲያቸው እንደማይመለከተው ያስታወቁት የምርጫ ስትራቴጂና ኮሚቴ ጽህፈት ቤት ኃላፊዋ፣ ምርጫው ዓለም አቀፍ መመዘኛዎችን ባያሟላ እንኳ ተቀባይነት ያለው ምርጫ እንዲሆን ቢያንስ አራት መመዘኛዎችን ማሟላት እንደሚኖርበት ተናግረዋል፡፡

ፖለቲካ ፓርቲዎች በነጻነት ተንቀሳቅሰው ሀሳባቸውን መሸጥ እንዳለባቸው፣ መራጩ ሕዝብ ሳይፈራ የሚመርጥበት ሀገራዊ ድባብ መፍጠር እንደሚያስፈልግ፣ ምርጫ ቦርድና ከምርጫ ጋር ግንኙነት ያላቸው የፌደራልም፣ የክልልም፣ የወረዳ አካላትና ሌሎች ባላድርሻዎች ፖለቲካ ፓርቲዎችን በፍትሐዊነትና በእኩልነት ሊመለከቱና ሊያስተናግዱ እንደሚገባና ሕዝቡ ድምፁን ከሰጠ በኋላ ድምፁን በንፅህና መቁጠር እንደሚያስፈልግ ያስረዱት ከውሰር እድሪስ፣ ምርጫ 2013 ሀገሪቷ ካለችበት ሁኔታ አንጻር ሌሎች ዓለም አቀፍ መመዘኛዎችን ባያሟላ እንኳ ከላይ የተጠቀሱትን አራት መመዘኛዎች ሊያሟላ እንደሚገባ አጽንኦት ሰጥተው ተናግረዋል፡፡መንግሥት በለመደው መልክ እቀጥላለሁ ካለ ሀገሪቷን የባሰ ችግር ውስጥ ስለሚከታት ምርጫው ሀገሪቷን ከባሰ ሁኔታ ወደ ተሻለ ሁኔታ ማሻገር የሚቻልበት ምርጫ መሆን እንዳለበት አሳስበዋል፡፡

ኢዜማ በ2013 ምርጫ መዋቅሩን በዘረጋባቸው 435 የምርጫ ወረዳዎች ላይ እጩዎችን በማቅረብ የሚወዳደር ይሆናል፡፡





# ኢዜማ በያዝነው ሳምንት ማብቂያ ላይም ዕጩዎችን ማስመረጡን የሚቀጥል ይሆናል

ጥር 12 ቀን 2013 ዓ.ም (የዜጎች መድረክ)

የኢትዮጵያ ዜጎች ለማኅበራዊ ፍትህ (ኢዜማ) ምርጫ 2013 ላይ ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እና ለክልል ምክር ቤት ወክለውት የሚወዳደሩ ዕጩዎችን ከጥር 01 ቀን 2013 ዓ.ም ጀምሮ ማስመረጥ መጀመሩ የሚታወቅ ነው፡፡ ኢዜማ ባሳለፍነው ቅዳሜ ጥር 08 ቀን 2013 ዓ.ም እና ጥር 09 ቀን 2013 ዓ.ም ዕጩዎቹን ሲያስመርጥ የዋለ ሲሆን፣ የፊታችን ቅዳሜ ጥር 15 ቀን 2013 ዓ.ም እና እሁድ ጥር 16 ቀን 2013 ዓ.ም ዕጩዎቹን ማስመረጡን የሚቀጥል ይሆናል፡፡

ዕጩዎቻቸውን ያላስመረጡ ምርጫ ወረዳዎችም የፊታችን ቅዳሜ ጥር 15 ቀን 2013 ዓ.ም እና እሁድ ጥር 16 ቀን 2013 ዓ.ም ዕጩዎቻቸውን የሚያስመርጡ ሲሆን ኢዜማን ወክለው በክልል ምክር ቤትም ሆነ በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የሚወዳደሩ ሁሉም ዕጩዎችም እስከ ጥር 16 ቀን 2013 ዓ.ም ድረስ ይታወቃሉ ተብሎ ይጠበቃል፡፡ ባሳለፍነው ቅዳሜና እሁድ ከአዲስ አበባ ውጪ በኦሮሚያ፣ አማራ እና ደቡብ ክልሎች የሚገኙ ምርጫ ወረዳዎችም ኢዜማን የሚወክሉ ዕጩዎች ማስመረጥ ችለዋል፡፡

ዕጩዎቻቸውን ያስመረጡ ምርጫ ወረዳዎች፣ የዕጩዎችን ሰነዶች መላካቸውንና ዕጩዎቹ በጉባኤ የተመረጡ መሆናቸውንና አስመራጭ ኮሚቴዎች ሰነዶቹ ላይ የፈረሙባቸው መሆናቸውን የማረጋገጡን ሥራም ድርጅት ጉዳይ ቋሚ ኮሚቴ እየከወነው ይገኛል፡፡

እስካሁን በተካሄደው ምርጫ ላይ ቅሬታ ያለው ማንኛውም አካል በወረዳው ላለው ዲሲፕሊን ኮሚቴ ቅሬታውን ማቅረብ የሚችል ሲሆን፤ በወረዳ ደረጃ ባለው የዲሲፕሊን ኮሚቴ ችግሩ ካልተፈታም ቅሬታውን በማዕከል ሥር ላለው የዲሲፕሊን ኮሚቴ ማቅረብ የሚቻልበት አሰራር ተዘርግቷል፡፡

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ይፋ ባደረገው የጊዜ ሰሌዳ መሠረት የዕጩዎች ምዝገባ ከየካቲት 08 ቀን 2013 ዓ.ም እስከ የካቲት 21 ቀን 2013 ዓ.ም የሚካሄድ ይሆናል ፡፡